


# አስደናቂው የዋሽንግቶን ዲ.ሲ. ሰላማዊ ሰልፍ ምን ያመለክታል?

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

September 19, 2016

በትላንቱ (September 19, 2016) ቀን በዋሺንግተን ከተማ የተካሄደው ሕዝባዊ ትእይንት (ሰላማዊ ሰልፍ) ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ፤ የኢትዮጵያን የሕዝብ፤ የኃይማኖት፤ የጾታ፤ የእድሜ እና ሌሎች ስርጭቶች የሚያንጸባርቅ ነበር። ከቴክሳስ፤ ከጅወርጅያ፤ ከኦሃዮ፤ ከንውዮርክ፤ ከማሳቹሴትስ፤ ከፔንሰልባንያና ሌሎች የአሜሪካ ግዛቶች በአውቶቡስና ሌሎች መጓጓዣዎች የመጡት ወገኖቻችን ድምጽን ለማሰማት ለተደረገው አስደናቂ ሰል ድምቀትና ውበት ሰጥተውታል።

ይህን ሰላማዊ ሰልፍ የተለየ የሚያደጋቸው መስፈርቶች ብዙ ናቸው። እኔ ትኩረት የምሰጠው ለሚከተሉት ነው፤

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን መለያው ማድረጉ፤

ሰልፉን ለማቀናበር ያስቻለው ቡድን ስፋትና ጥራት ያለው መሆኑ፤ ከቡድን ባሻገር ለአገርና ለወገን ተባብሮና ተናቦ ለመስራት መቻሉ "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" የሚለውን ብሂል በተግባር ማሳየቱ፤ የዚህ አይነት የመተባበር መንፈስና ተግባር ልምድ እንዲሆን ከሕዝብ ድምጽ መሰማቱ፤

ኦሮሞው፤ አማራው፤ ጉራጌው፤ አፏኩ፤ ሶማሌው፤ ወላይታው፤ ትግራዩ እና ሌላው ከብሄር፤ ከኃይማኖት፤ ከጾታ፤ ከእድሜና ሌላ መለያ ባሻገር ለአገርና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት፤ እኩልነት፤ ፍትህ እና ተቆርቋሪነት ማሳየቱ፤ የደመቀ ድምጽ ማሰማቱ፤

የሴቶች፤ የወጣቶች፤ የባላሞያዎች እና ሌሎች ተሳትፎ ከመቸውም የላቀ መሆኑ፤

የሕዝቡ ብዛትና የመፈክሮቹ አግባብነት ለአሜሪካ መዲና የተለየ ድምቀት መስጠቱ፤ መንገዶች ሁሉ ስለተዘጉ ተመልካቹ ሕዝብ ትእይንቱ ለምን እንደሆነ መጠየቁ፤ ትምህርትና ግንዛቤ ማግኘቱ፤ በቤቱ የሚነጋገርበት መሆኑ፤

አዘጋጆቹ ባወጡት እቅድ መሰረት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ለውጭ ጉዳይ የበላይ ኃላፊ ለሆኑት ለሴክረተሪ ጆን ኬሪ ጸሃፊ የተዘጋጀው ደብዳቤ በእጅ መሰጠቱ እና መመዝገቡ፤

የአሜርካ ምክር ቤት (ኮንግሬስ) በውሳኔ ላይ ከፍተኛ ሚና ስላለው H.R. 861 ሕጋዊ የሚሆንበትን ለማጠናከር በምክር ቤቱ ፊት ለፊት የደመቀ ንግግር እና መፈክር መሰማቱ፤ ለኢትዮጵና ለሕዝቧ ትኩረት ለሰጡት ለሴናተር ኮርከር፤ ሴናተር ካርደን፤ ለምክር ቤት አባላት ሮይስ፤

ኤንግል፤ ስሚዝ፤ ኮፍማንና ኤሊሰን የተጻፉት ደብዳቢዎች እንዲደርሷቸው መደረጉ፤

የተሳታፊዎች ድምጽና ለወገን ተቆርቋሪነት ስር እንደሰደደ፤ እና ሰልፈኛው ከአሁን በኋላ በያለበት ተከታታይ ስራዎችን ተባብሮ ለመስራት ቃል ኪዳን መግባቱ ሕዝባዊ ትእይንቱን የተለየ ያደርገዋል። በዚህ አጋጣሚ ይህን አስደናቂ ሕዝባዊ ትእይንት ስኬታማ ያደረጉትን የአስተባባሪ ቡድን አባልትና ድጋፍ የሰጡትን ሃያ አራት ድርጅቶች እንድታመሰግኗቸው ስማቸውን ከዚህ አጭር ዘገባ ጋር አያይዣለሁ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር! የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት በእኩልነት!